DEVELOPMENTAL DISABILITIES ADMINSTRATION (DDA)

# በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የዝውውር ስምምነት (VPA)
# የዕድገት አካለ ስንኩልነት ላለበት ልጅ ወይም ወጣት
# Voluntary Placement Agreement (VPA) For Child or Youth With Developmental Disabilities

ይሄ ስምምነት የፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የዝውውር አገልግሎቶችን (VPS) የሚመለከት በዕድገት አካለ ስንኩልነቶች አስተዳደር (DDA) እና በወላጅ /ጠባቂ መካከል የሚከተለውን በተመለከት የሚደረግ ነው:

| የልጁ/ልጅቷ ስም (መጀመሪያ፣ የአባት፣ የአያት) | የትውልድ ቀን | DDA መታወቂያ ቁጥር |
|---|---|---|
| | | |

ይሄንን ስምምነት በመፈረም፣ **DSHS / DDA እና በልጁ/በልጅቷ ወላጅ(ጆች) / ጠባቂ (ዎች) የሚከተለውን ለመፈጸም የተደረገ ነው:**

ሀ. በ RCW 71A.10.020 ላይ እንደተገለጸው ልጁ/ልጅቷ ከ 18 ዓመት በታች እና የዕድገት አካለ ስንኩልንት ችግር አለበት/ አለባት።“"የዕድገት አካለ ስንኩልነት (Developmental disability) ማለት ከእውቀት አካለ ስንኩልነት፣ ሴሬብራል ፓልሲ፣ ራስ መጣል፣ ኦቲዝም፣ ወይም ሌላ ኒውሮሎጂካል ወይም ከዕውቀት አካለ ስንኩልነት ጋር በጥብቅ የተያያዘ እንደሆነ በፀሐፊው የተገኘ ሁኔታ ወይም ከዕውቀት አካለ ስንኩልነት ያለባቸው ግለሰቦችን ጋር የሚመሳሰል የሕክምና እገዛ የሚያስፈልገው፣ ግለሰቡ የአስራ ስምንት ዕድሜ ሳይሞለው አካለ ስንኩልነቱ የተከሰተ እንደሆነ፣ እየቀጠለ ያለ እንደሆነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ እንደሚቀጥል የሚጠበቅ ከሆነ፣ እና በግለሰቡ ላይ ከፍተኛ ጉድለት የሚያስከትል ከሆነ ነው) እና

ለ. ወላጁ ወይም ጠባቂው ሕጋዊ የማሳደግ መብት ያለው እንደሆነ እና ከልጁ/ልጅቷ ማሳደግ ጋር በተያያዘ ምንም ዓይነት እየታየ ያለ የጥቃት ችግር እና ችላ ማለት የሌለ እንደሆነ ፟እና

ሐ. ከቤት ውጪ ዝውውሩ በልጁ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ እና በልጁ የዕድገት አካለ ስንኩልነት የተነሳ ብቻ ሲሆን ነው።

ልጅ የህንድ ዝርያ ይኖረዋል ተብሎ የሚታመንበት ምክንያት አለ? ☐ አዎ ☐ አይደለም

አዎ ከሆነ፣ በህንዳዊ የልጅ ድጎማ መመሪያ ላይ ያሉትን መመሪያዎች ይከተሉ። ልጁ/ልጅቷ የሚከተለውን ከሆነ/ከሆነች ይሄንን ቅጽ አይጠቀሙ: 1) በፌደራል የሚይታወቅ የህንድ ጎሳ አባል ከሆነ፥ ወይም 2) በፌደራል ዕውቅና በተሰጠው የሕንድ ጎሳ አባልነት ብቁ ከሆነ እና የልጁ በውልደት ያገኛቸው ወላጆቹ የጎሳ ዓባል የሆኑ እንደሆነ። ከልጁ/ልጅቷ ውልደት አስር (10) ቀን በኋላ ከጎሳ ወይም የወጣት ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፊት በወላጅ ስምምነቱ ከተፈረመ እና በዳኛው ስምምነቱ የፀደቀ ካልሆነ በስተቀር ለማደጎ ማሳደጊያዎች ለሚሰጡ በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረቱ ስምምነቶች የፀኑ አይሆኑም። በሕንዳዊ ልጅ ወላጅ ወይም በሕንዳዊ ጠባቂ ለማደጎ ማሳደጊያ መስጠት ስምምነት ይጠቀሙበት።

**<u>ወላጅ / ጠባቂ የሚስማማው</u>:**

እኔ በፍቃደኝነት ከላይ ስሙ የተጠቀሰው ልጅ በማደጎ ውስጥ እንዲያድግ እና በ DSHS/DDA ክትትል እንዲደረግለት እስማማለሁኝ። **የልጄን ጠባቂነት መብቴን እንደያዝኩኝ እቆያለሁኝ።** ድንገተኛ ያልሆነ ቀዶ ጥገና እና የዘውትር ሕክምና እንክብካቤን የመፍቀድ ስልጣኔን፣ ጋብቻ ላይ የመስማማት፣ በመከላከያ ኃይሎች ጋር የመቀላቀል፣ እና ለልጄ ሌሎች አስፈላጊ የሕግ ውሳኔዎችን የመወሰን ስልጣኔን እንደያዝኩኝ እቆያለሁኝ። የተፈቀደለት ተወካይ ከፋይ ልጄ ለማግኘት ብቁ የሆነባቸውን ማንኛውንም ጥቅማጥቅሞች እንዲያስተዳድር እና ለልጄ የማሳደጊያ እና ለሚቀርቡት አገልግሎቶች (የይግባኝ ጠያቂ ወይም የሌላ ሰው ዓረፍተሐሳብ ይመልከቱ) የሚወጡትን ወጪዎች እንዲሸፍን እነዚህን ገንዘቦች እንዲጠቀምባቸው እፈቅዳለሁኝ። ይሄ ስምምነት በጽሁፍ በማስገባው ማመልከቻ ሊቋረጥ እንደሚችል ግንዛቤው አለኝ። እንደዚሁም በ RCW 13.34.050 ወይም 26.44.050 በተያያዘ ወደ ጥበቃ ካልተወሰደ፣ በ RCW 13.34.060 መጠለያ ላይ ካልተወሰደ፣ ውይም RCW 13.34.130 የማደጎ ማሳደጊያ ካልተወሰደ በስተቀር DDA የጽሁፍ ጥያቄ ከቀረበለት በኋላ በ 72 ሰዓታት ውስጥ ልጄ እንደሚመለስልኝ እስማማለሁ እና አውቃለሁኝ። **እንደዚሁም የልጄን የአሳዳጊነት መብቴ ስለሚጠበቅልኝ፣ የልጄ ማደጎ መሰጠት የሚቋረጥ ከሆነ እና ሌላ ተገቢ የማሳደጊያ ቦታ ከሌለ፣ ተገቢ የማሳደጊያ ስፍራ እስኪገኝ ድረስ ወደ ቤቴ መልሼ መውሰድ እንዳለብኝ አውቃለሁኝ።** ለ DDA ፈቃድ ሰጥቻለሁኝ እና ከታች እንደተገለጸው የሚከተሉትን ተግባራት እና ሃላፊነቶችን ለመወጣት እስማማለሁኝ:

1. ለ DDA ወቅታዊ አድራሻዬን እና ስልክ ቁጥሬን ማሳወቅ እንዳለብኝ፡
2. ውሳኔዎችን መወሰን ላይ ከ DDA ሠራተኞች እና ልጌን ከሚንከባከቡ ሰዎች ጋር ለመሳተፍ እና በትብብር መስራት፥
3. ከልጄ ጋር የግል ግንኙነት መፍጠር እና ፈቃድ ከተሰጠው አቅራቢ ጋር “የጋራ የማሳደግ ዕቅድ” ን በጋራ የመቅረጽ እና የመከታተል ተሳትፎ ማድረግ፥
4. ለልጄ አስፈላጊው ድጋፍ መቅረቡን ለማረጋገጥ ለ DDA የሕክምና፣ ማህበራዊ፣ አካላዊ፣ ባህሪያዊ፣ የወንጀል፣ እና የትምህርት መረጃን ለማቅረብ፥
5. በማህበራዊ ደህንነት አስተዳደር በኩል የልጄን ሙሉ ጥቅማጥቅሞችን በማግኘት ላይ ከ DDA ጋር ለመተባበር። እነዚህ ፈንዶች (የልጅ እና/ወይም የጉዲፈቻ ድጋፍን ሊያካትት ይችላል) የልጄን መሰረታዊ የክፍል እና የመኖሪያ ወጪዎችን ለመክፈል እንደሚያገለግሉ እረዳለሁኝ እና እስማማለሁኝ፥
6. በዋሽንግተን ግዛት ውስጥ ወይም በ WAC 182-501-0175 ላይ እንደተጠቀሱት ከግዛት ውጪ ያሉ አጎራባች ከተማዎች ውስጥ መኖሬን እቀጥላለሁኝ፥
7. በግል የጤና እና የጥርስ መድህን (የሚተገበር ከሆነ) ውስጥ የልጄን መግባት ዘላቂ ማድረግ፥ እና
8. ለ DDA በፍርድ ቤት የታዘዘውን የጋራ የልጅ የማሳደግ ዕቅድ ቅጂውን ወይም/እና የሚተገበር ከሆነ የፍቺ ማጽደቂያውን ማቅረብ።

**DDA በማደጎ ውስጥ ሲገባ የሚከተሉትን ለማድረግ ይስማማል:**

1. በተቻለ መጠን የልጁን/የልጅቷን የግለሰብ እና የባሕል ፍላጎቶችን የሚያሟላ ፈቃድ ያለው መኖሪያ ቤት ወይም ተቋም ውስጥ ልጁን ለማቆየት፥
2. ለልጁ/ለልጅቷ ግለሰባዊ የድጋፍ ዕቅድ ከወላጅ/ጠባቂ ጋር በጋራ ለመንደፍ እና ተገቢውን የሚገኙትን አገልግሎቶች ለማቅረብ፥
3. እንደ ወላጅ መብትዎን እና ግዴታዎን እንዲከበርልዎ ያግዛል፥
4. ከቤት ውጪ በማሳደጊያ ውስጥ መሆኑ/መሆንዎ ለልጁ/ለልጅቷ የላቀ ጥቅም ሲባል እንደተደረገ እና በልጁ የዕድገት አካለ ስንኩልነት የተነሳ ብቻ ስለመሆኑ ዓመታዊ የፍርድ ቤት ውሳኔን ማግኘት፥ እና
5. Tለወላጅ/ ጠባቂው ሰለ ልጁ/ልጅቷ እንክብካቤ፣ አስተዳደግ እና የጤና ሁኔታ ማሳወቅ፥

**የዚህ ስምምነት ጉድለቶች:**

1. DSHS የጽሁፍ ማስታወቂያ በመስጠት ወይም የፍርድ ቤት ክስ በመጀመር በማንኛውም ሰዓት ይሄንን ስምምነት ለማቋረጥ ይችላል፥
2. ይሄ ስምምነት የሚጀምረው በ ____________________።
3. ከተሰጠው ጊዜ በፊት፣ የወጣቶች ፍርድ ቤት ለልጁ/ልጅቷ የላቀ ጥቅም ሲባል በማሳደጊው ውስጥ እንዲቆይ ለመወሰን የሚገመግም ካልሆነ በስተቀር፣ ከ 180 ቀናት በላይ ልጁ በማሳደጊያው ስፍራ ውስጥ አይቆይም። ሁሉንም የፍርድ ቤት ክስ የሚሰሙበትን ቀናት እንዲያውቁ ይደረጋሉ። ፍርድ ቤቱ ቀጣይ በማሳድጊያ ቤት ውስጥ የማቆየት ሂደት ለልጁ የላቀ ጥቅም እንደማይሰጥ ያመነበት እንደሆነ፣ በማሳደጊያ ውስጥ የማቆየቱ ስምምነት ይቋረጣል።
4. ይሄ ስምምነት በተዋዋይ ወገኖቹ ከዚህ ቀደም የተደረጉ ማናቸውም የ VPA ውሎች በላይ በከፍተኛ ደረጃ ይታያል።

| | |
|---|---|
| የወላጅ/ጠባቂ ፊርማ | ቀን |
| የወላጅ/ጠባቂ ፊርማ | ቀን |
| የ DDA ማህበራዊ ጉዳይ ሠራተኛ/ የማህበራዊ አገልግሎት ስፔሻሊስት ፊርማ | ቀን |

I, __________________________, (የወላጅ ስም ይታተም) የልጁን የማሳደግ ሕጋዊ መብት እንዳለኝ ወይም በማሳደግ ኦቅድ ውስጥ እንደተጠቀሰው ልጁ በአብዛኛው ከእኔ ጋር እንደሚኖር፣ ወይም በማሳደግ ዕቅድ ውስጥ ከዚህ ስምምነት ጋር የመስማማት መብት በተሰጠኝ መሰረት በፍትሐብሔር ሕግ መሰረት የሚከተለው እውነት እንደሆነ እና ትክክለኛ , ሰለመሆኑ አረጋግጣለሁኝ።

______________________________ በ __________________ ላይ ________________________
የወላጅ/ጠባቂ ፊርማ ቀን ቦታ (ከተማ፣ ግዛት)

# የይገባኛል ጠያቂ ወይም ሌላ ሰው መሐላ
## Statement of Claimant or Other Person

| የደሞዝተኛ ስም፣ የራሱን ሥራ የሚሰራ ግለሰብ፣ ወይም የ SSI ይገባኛል ጠያቂ ስም | የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር |
|---|---|
| መሐላውን የሚፈጽመው ሰው ስም (ከላይ ከተጠቀሱት ደሞዝተኛ፣ የራሱን ሥራ የሚሰራ ግለሰብ፣ ወይም የ SSI የጥገባኛል ጠያቂ ውጪ ከሆነ) | ከደሞዝተኛ ፣ የራሱን ሥራ የሚሰራ ግለሰብ ወይም የSSI ይገባኛል ጠያቂ ጋር ያለው ዝምድና |

ይሄ መሐላ ለማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር አገልግሎት እንደሚውል በመረዳት፣ እንደሚከተለው እማኝነቴን እሰጣለሁኝ:

**በፍትሕብሔር ሕግ መሰረት በዚህ ቅጽ፣ በማንኛውም ተጓዳኝ መሐላዎች ወይም ቅጾች ላይ የቀረቡትን ሁሉንም መረጃዎች እንደመረመርኩኝ፣ እና እኔ እስከማውቀው ደረስ እውነተኛ እና ትክክለኛ ስለመሆኑ አረጋግጣለሁኝ። በዚህ መረጃ ውስጥ ጠቃሚ መረጃን በሐሰት ወይም በሚያሳስት መልኩ ሆን ብሎ የሚያቀርብ፣ ወይም ሌላ ሰው እንደዛ እንዲያደርግ የሚገፋፋ ማንኛውም ሰው፣ ወንጀል እንደፈጸመ እና እስር ቤት ውስጥ ሊገባ እንደሚችል፣ ወይም ሌሎች ቅጣቶችን ወይም ሁለቱንም ሊጋፈጥ እንደሚችል አውቃለሁኝ።**

**መሐላውን የሚፈጽመው ግለሰብ ፊርማ። በቀለም ይፃፍ።**

| የወላጅ / ጠባቂ ፊርማ (የመጀመሪያ ስም፣ የአባት ስም ምህፃር፣ የአያት ስም)<br>እዚህ ይፈርሙ ▶ | ቀን (ወር፣ ቀን፣ ዓመት)<br>ስልክ ቁጥር (የአካባቢ መለያ ኮድ ያስገቡ) |
|---|---|
| የፖስታ አድራሻ (ቁጥር እና መንገድ፣ የአፓርታማ ቁጥር፣ ፓ.ሳ.ቁጥር የገጠር መንገድ) | |
| ከተማ እና ግዛት | ዚፕ ኮድ |

| የወላጅ / ጠባቂ ፊርማ (የመጀመሪያ ስም፣ የአባት ስም ምህፃር፣ የአያት ስም)<br>እዚህ ይፈርሙ ▶ | ቀን (ወር፣ ቀን፣ ዓመት)<br>ስልክ ቁጥር (የአካባቢ መለያ ኮድ ያስገቡ) |
|---|---|
| የፖስታ አድራሻ (ቁጥር እና መንገድ፣ የአፓርታማ ቁጥር፣ ፓ.ሳ.ቁጥር የገጠር መንገድ) | |
| ከተማ እና ግዛት | ዚፕ ኮድ |

ከላይ በ (X) ምልክት መሐላው ከተፈረመ ብቻ ምስክሮች ያስፈልጋሉ። በ (X) ምልክት ከተፈረመ፣ መፈራረሙ ላይ ግክለሰቡን የሚያውቁ ሁለት ምስክሮች ከታች ሙሉ አድራሻቸውን በመስጠት መፈረም አለባቸው።

| 1. የምስክር ፊርማ | 2. የምስክር ፊርማ |
|---|---|
| አድራሻ (ቁጥር እና መንገድ፣ ከተማ፣ ግዛት፣ እና ዚፕ ኮድ) | አድራሻ (ቁጥር እና መንገድ፣ ከተማ፣ ግዛት፣ እና ዚፕ ኮድ) |